# እገዛና መረጃ ለማግኘት

## የትራንዚት ጉዞ መረጃ

**King County Metro Transit**
የጉዞ መረጃ (206) 553-3000
www.kingcounty.gov/metro
Twitter @kcmetrobus

**Community Transit**
(425) 353-7433 (RIDE)
www.communitytransit.org
Twitter @MyCommTrans

**Pierce Transit**
(253) 581-8000
www.piercetransit.org
Twitter @PierceTransit

**Sound Transit**
1 (888) 889-6368
www.soundtransit.org
Twitter @SoundTransit

**Amtrak**
1 (800) 872-7245
www.amtrak.com

## ት/ቤቶች

ትቤቶች የሚዘጉባቸውን ቀናትና የፕሮግራም ለውጦችን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የአካባቢውን የራዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢዎች ይከታተሉ። የአካባቢው ት/ቤት የበረዶ ሁኔታን በተመለከተ የሚያሰራጨውንም መረጃ መከታተልዎን ርግጠኛ ይሁኑ።

**Seattle Public Schools**
www.seattleschools.org
Twitter @seapubschools

## አማራጭ ቋንቋዎች

ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጭ ያሉ ቋንቋዎችን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት
www.seattle.gov/transportation/winterweather.htm

## የመንገድ ጥገና

**Seattle Department of Transportation**
(206) 684-7623 (ROAD)
www.seattle.gov/transportation
Twitter @seattledot

**King County Road Services Division**
የመንገድ ጥገና (206) 296-8100
www.kingcounty.gov/transportation/kcdot/roads

በከተማ ዳርቻ ያሉ ከተሞች
በከተማዎ ውስጥ ለሚገኙ የሕዝባዊ ስራዎች ወይም የመንገድ መምሪያ ስልክ ይደውሉ።

## የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥ

**Seattle City Light**
(206) 684-3000
www.seattle.gov/light
Twitter @SEACityLight

**Puget Sound Energy**
1 (888) 225-5773
www.pse.com
Twitter @PSETalk

## አውራ ጎዳና እና የጀልባ ትራንስፖርት ሁኔታ

**Washington State Department of Transportation**
ለግዛት መስመሮች የመንገድ ሁኔታዎች፣ በዚህ ይደውሉ፡ 511
www.wsdot.wa.gov/traffic
Twitter @wsdot_traffic

**Washington State Ferry Information**
ለግዛት አቀፍ፣ በዚህ ቁጥር ይደውሉ፡ 511
ሲያትል ውስጥ (አውቶማቲክ) (206) 464-6400
www.wsdot.wa.gov/ferries
Twitter @wsferries

**2019-2020**

Seattle Department of Transportation

# የክረምት አየር ሁኔታ





AMHARIC

## የክረምት አውሎ ነፋስ - ዕቅዳችን ይህን ይመስላል

ሲያትል ውስጥ፣ በክረምት ወቅት ከባድ ዝናብ፣ ኃይለኛ ነፋስና በረዶ ሊኖር ይችላል፡፡

- ሰራተኞቻችን በቀን ለ24 ሰዓት እንደዚሁም ዓመቱን በሙሉ የአየር ሁኔታ ሪፖርትን የሚከታተሉ ሲሆን ከብሔራዊ የአየር ሁኔታ አገልግሎት ጋር የሚያገናኝ የቀጥታ መስመር እና የራዳር መረጃ ጋር ግንኙነት አላቸው፡፡
- ከዩኒቨርሲቲ ኦፍ ዋሽንግተን ጋር በመሆን የተዘጋጀ የአየር ሁኔታ ትንበያ መሳሪያ የምንጠቀም ሲሆን የዚህ መሳሪያ ስም ስኖውዋች (SNOWWATCH) ይባላል፣ አገልግሎቱም አውሎ ነፋስ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ ሊያደርሰው የሚችለውን ውጤት ለማወቅ ነው፡፡ ይህ መረጃ ሰራተኞቻችን አገልግሎታቸው የሚፈለግበትን ዋነኛ ቦታ ለመወሰን ያገለግላል፡፡
- በከተማ ድልድዮች ላይ የተገጠሙ ኮምፒውተራይዝድ አነፍናፊዎች (ሴንሰሮች) እና መሬት ላይ የተተከሉ አነፍናፊ መሳሪያዎች ወቅቱን የጠበቀና ትክክለኛ የሆነ የአየር እና የመንገድ ሽፋን የሙቀት መጠን መረጃ ይሰጣሉ፡፡
- በተመረጡ ዋና ዋና መንገዶች ላይ ያሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎች ለማየት ፈጣንና ወዲያውኑ መረጃ የሚልኩ ካሜራዎችን እንጠቀማለን፡፡ የካሜራዎቹን ዕይታ ከቀጣዩ የኤስዲኦቲ ድረ-ገጽ ማየት ይችላሉ፡ www.seattle.gov/travelers.

የሲያትል ከተማ የበረዶ ግግርን ለመከላከል ምርጥ የተባሉ አሰራሮችን በመጠቀም የቅድመ ጥንቃቄ አሰራርን ይከተላል፡

- የኤስዲኦቲ ሰራተኞች የመንገድ መጥረጊያና የጨው መርጫ የተገጠመባቸውን ተሽከርካሪዎች በመጠቀም ዋና ዋና መንገዶች ከአደናቃፊ ነገሮች የጸዱ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡
- በረዶ መዝነብ ከመጀመሩ በፊት፣ ሰራተኞች የበረዶ ግግር እንዳይኖር ለመከላከል የበረዶ ማቅለጫ በመጠቀም ዋና ዋና መንገዶችና ድልድዮች ላይ የቅድመ መከላከል እርምጃ ይወስዳሉ፡፡
- በረዶው መዝነብ ሲጀምር፣ ሰራተኞች በመስመራቸው በኩል በማለፍ እንዳስፈላጊነቱም ጨው በመርጨት መንገዶችን የማጽዳት ስራ ይሰራሉ፡፡ በግምት ወደ አንድ ኢንች የሚደርስ የበረዶ ቁልል ሲፈጠር የመጥረግ ስራቸውን ይጀምራሉ፡፡
- መንገዱ በበረዶ በሚሸፈንበት ወቅት የግሎባል ፖዚሺኒንግ ሳተላይት (ጂፒኤስ) ሲስተም ተሽከርካሪዎቹ የት እንደሚገኙ ቦታቸውን ያመለክታል፡፡ በኤስዲኦቲ ድረ ገጽ ላይ ያለ ካርታ ተሽከርካሪዎቹ በአሁኑ ሰዓት የት እንደሚገኙና በተሽከርካሪዎቹ የተጸዱት መንገዶች የትኞቹ እንደሆኑ ያሳያል፡፡ አውሎ ነፋስ በሚከሰትበት ወቅት በቀጣዩ ድረ ገጾችን ላይ ካርታውን ማየት ይችላሉ፡ web6.seattle.gov/sdot/winterweathermap.

## አውሎ ነፋስ ወደእኛ አቅጣጫ ሲመጣ - እንዘጋጃለን

ዋና ዋና መንገዶችን እናፀዳለን፡፡ እነዚህ መንገዶች እንደ ሆስፒታልና ት/ቤቶች፣ ለፖሊስ፣ ለእሳት አደጋ መከላከያ ተሽከርካሪዎችና አውቶብሶች አገልግሎት ወደሚሰጡና በሲያትል ከተማ ወደሚገኙ ዋና ዋና ቀጣሪ ድርጅቶች የመሳሰሉ ወሳኝ ሕዝባዊ ተቋማት ጋርየሚያደርሱ ናቸው፡፡ አውራ ጎዳናዎችን አናፀዳም፡፡

- ለክረምቱ ወቅት መዘጋጀት የጀመርነው በበጋ ወቅት ነው፡ ሰራተኛን ማሰልጠን፣ መሳሪያዎችን ለስራ ዝግጁ ማድረግና ከአካባቢው የኤጀንሲ አጋሮች ጋር መስራት አለብን፡፡
- ኃይለኛ ነፋስ ወይም ከባድ ዝናብ እንደሚኖር ከተተነበየ፣ ሰራተኞቻችን የወዳደቁ ዛፎችን ከመንገድ ላይ ለማንሳት እና የመንገድ ዳር ምልክቶችን ለመጠገን ዝግጁ ናቸው፡፡
- የጨው እና ፈሳሽ የበረዶ ማቅለጫ አቅርቦታችን በዋና ዋና መንገዶችና ድልድዮች ላይ በረዶ እንዳይጋገር ለመከላከል ዝግጁ ናቸው፡፡

## ጠቃሚ መረጃዎችን የያዘ የኤስዲኦቲ ድረ ገጽ

www.seattle.gov/transportation/winterweather.htm
https://takewinterbystorm.org/
www.seattle.gov/travelers
Twitter @SDOTtraffic
sdotblog.seattle.gov
www.seattletraffic.org

## ሲያትል መጨናነቅ - የጉዞ ተፅዕኖዎች

ከዊንተር ወራት በኋላ አመቱን በሙሉ ተጓዦች እንዴት እንደሚዘዋወሩ በጣም እየተለዋወጠ ነው፡፡ የ Seattle ከተማ አዲስ የትራፊክ መጨናነቅ ዘመን አጋጥሞታል፡፡ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ውስጥ የ Seattle መሀልከተማ በእድገት ላይ ያለውን የከተማችንን ፍላጎት ለማሟላት ሽግግር ያደርጋል፡፡ የመጓጓዣ ኢንጂነሮቻችን ይህን የሽግግር ደረጃ የሲያትል የመጨናነቅ ወቅት ብለው ስም አውጥተውለታል፡፡ በዘህ ወቅት በመሀል ከተማው ውስጥ እና ዙሪያ የሚጓጓዙ ሰዎች በበርካታ ግንባታ ምክንያት ይቸገራሉ፤ ይህ ደግሞ ተጨማሪ መንገዶች እንዲዘጉ ስለሚያደርግ እና የስራ መራዘምን ስለሚያስከትል የበለጠ ይጨናነቃል፡፡

**ጉዞዎን ለመቀየር መውሰድ ያለቦት አምስት ቀላል እርምጃዎች ምንድን ናቸው?**

1. ለወደፊቱ እቅድ ያውጡ እና በከተማው ጎዳናዎች ላይ ተጨማሪ ትራፊክ ይጠብቁ፡፡
2. ያሰቡበት ቦታ ለመድረስ ለራስዎ ተጨማሪ ጊዜ ይስጡ፡፡
3. እንደ በእግር መሄድ፣ ብስክሌት መንዳት ወይም አውቶቡስ ወይም ቀላል ባቡር ያሉ አዲስ የመጓጓዣ ሁኔታ ይሞክሩ፡፡ ከተቻለ መንዳት ያቁሙ፡፡
4. በሲያትል ስኩዊዚ ወቅት የሚያስፈልግዎን መሳሪያ እና መረጃ ለማግኘት www.seattle.gov/traffic ይጎብኙ፡፡
5. እንደእርስዎ ላሉ ተጓዦች ታጋሽ እና ደግ ይሁኑ፡፡ ሁላችንም እዚህ ውስጥ አንድ ነን!

በዚህ ከባድ የትራፊክ መጨናነቅ ወቅት የሲያትል ከተማ እና WSDOT በተቻለ መጠን ችግሮችን ለመቀነስ በጋራ እየሰሩ ነው፡፡

## ከመንገድ ዳርቻዎች ልም በረዶንና ርግ በረዶን ማስወገድ

የፓጀት ሳውንድ ኮንቨርጀንስ ዞን እንደዚ ሊገመቱ የማችሉትን የአየር ፀባይን ስለሚፈጥር፥ በቅርባችን ያለውን ትክክለኛ ክፍት መንገዶችን ለማፅዳት ነዋሪዎች ላይ እንመሰረታለን፡፡ በእርግጥም፥ የሲያትል መዛጋጃ ኮድ ቁጥር (Title) 15 የንብረት ባለበቶችና ኮንትራክተሮች በቅርባቸው የሚገኘውን የህዝብ መንገድ እንዲያፀዱ ወይም እንዲጠግኑ ይጠይቃል፡፡

በቁጥር (Title) 15 ስር፥ በግል ንብረት አጠገብ ያሉትን መንገድ ዳርቻዎችንና ሌሎችን የህዝብ መንገዶች መሰረቶችን በወቅቱ መንከባከብ የንብረት ባለበቱ ወይም በይዞታነት የያዘው ( እንደ እኔ ኮንትራክተር ያሉት) ኃላፊነት ነው፡፡  ልም በረዶ ወዴ ርግ በረዶ ከመቀየሩ በፊት ማፅዳት በጣም ተመራጭና  አካፋንና አንነድ ከረጢት የመንገድ ጨው በእጅ መያዝ ጥሩ ዊንተር ዝግጅት ነው፡፡

# ካርታው የሚያሳየው መረጃ

(እባክዎ በሁለቱ ገጾች ላይ የተያያዘውን ካርታ ይመልከቱ፣ የከተማው ሰሜናዊ ከፊል እና ደቡባዊ ከፊል።)

የኤስዲኦቲ የበረዶ መስመሮች የሚያሳዩት ለእያንዳንዱ መንገድ የታቀደውን የአገልግሎት ደረጃ እንጂ በቅድሚያ የሚጠረጉት መንገዶች የትኞቹ እንደሆኑ አይደለም። በሲያትል ከተማ ውስጥ ለሚገኙና በከተማው መንግስት ጥገና ለሚደረግላቸው በጣም ወሳኝ ለሆኑ መንገዶች ከፍተኛ ደረጃ ያለው አገልግሎት እንሰጣለን። ክፍለ ግዛቱ በሲያትል ከተማ ውስጥ የሚገኙ I-5 እና በርካታ ድልድዮችን ይጠግናል። እነዚህ መንገዶች የተመረጡበት ምክንያት የሲያትልን አጎራባች አካባቢዎች ከመሃል የከተማው ክፍልና ከታላቁ የፑጌት ሳውንድ ክልል (Puget Sound region) ጋር የሚያገናኙ በመሆናቸው ነው። እነዚህ መንገዶች ሆስፒታልና ት/ቤት ወደመሳሰሉ በጣም ወሳኝ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዘንድ የሚያደርሱና የፖሊስ፣ የእሳት አደጋ መከላከያ ተሽከርካሪዎች እና አውቶብሶች ብዙውን ጊዜ የሚገለገሉባቸው እና ወደ ዋና ዋና ቀጣሪ ድርጅቶች የሚያደርሱ መንገዶች ስለሆኑ ነው። ከተማ አቀፍ የበረዶ ነፋስ ሲከሰት፣ የኤስዲኦቲ ስትራቴጂ የትራፊክ እንቅስቃሴው እንዳይስተጓጎል ሁለቱም ዓይነት ደረጃ ያላቸውን መንገዶች ማጽዳት ይሆናል።

ያስታውሱ፣ ኤስዲኦቲ ከዋና መንገድ ውጭ ያሉ መንገዶችን አያፀዳም።

# የአገልግሎት ደረጃ

ከዚህ ጋር የተያያዘው ካርታ ጎልድ እና ኤመራልድ ተብለው የሚጠሩ የበረዶ መንገዶችን የተለያዩ ምድቦችን የሚያሳይ ነው።

ጎልድ የበረዶ መስመር: እነዚህ መንገዶች ለሆስፒታሎች፣ አውቶብሶች፣ ትልልቅ የጭነት መኪናዎች እና ለዋና ዋና ቀጣሪ ድርጅቶች ወሳኝነት ያላቸው ናቸው። የኤስዲኦቲ አላማ አውሎ ነፋስ ተከስቶ ሁኔታው ከተረጋጋ በኋላ በ12 ሰዓት ጊዜ ውስጥ የተስተካከለ የመንገድ ንጣፍ በሁሉም የጉዞ መስመሮች ላይ እንዲኖር ማድረግ ነው።

ኤመራልድ የበረዶ መስመር: እነዚህ መንገዶች ለሆስፒታሎች፣ ለአውቶብሶችና ለአጠቃላይ ትራፊክ ከተማ አቀፍ ወሳኝነት ያላቸው ናቸው። የኤስዲኦቲ አላማ አውሎ ነፋስ ተከስቶ ሁኔታው ከተረጋጋ በኋላ በ12 ሰዓት ጊዜ ውስጥ የተስተካከለ የመንገድ ንጣፍ በያንዳንዱ አቅጣጫ በአንድ የጉዞ መስመር ላይ እንዲኖር ማድረግ ነው።

# ከአውቶብስ ሲስተም ጋር በቅንጅት መስራት

ኤስዲኦቲ እና የኪንግ ካውንቲ ሜትሮ ትራንዚት የኤስዲኦቲ የበረዶ መንገዶች የትራንዚት ተጠቃሚውን ሕዝብ ፍላጎት የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስራቸውን በጥንቃቄ ሲያከናውኑ ቆይተዋል። የበረዶ መንገዶች ከሚባሉት መካከል በሚጥልበት ወቅት የሜትሮ አውቶብሶች የሚጠቀሙባቸው መንገዶች ይገኙበታል።

# ሌሎች መንገዶች

የኤስዲኦቲ ሰራተኞች ሊያጸዷቸው ወይም ጨው ሊያፈሱባቸው የማይችሉ አንዳንድ መንገዶች አሉ። እነዚህ መንገዶችም ብዙ ጉዞ የማይደረግባቸው መንገዶች፣ በረዶ በሚጥልበት ወቅት ለሕዝብም ሆነ ለኤስዲኦቲ ተሽከርካሪዎች ብዙ ጊዜ አስተማማኝ ያልሆኑ የዳገት ላይ መንገዶች ናቸው።

በረዶ በሚጥልበት ወቅት ለማሽከርከር አስተማማኝ ያልሆኑት ዳገታማ መንገዶች የትኞቹ እንደሆኑ ሰራተኞቻችን ያውቃሉ: : ሰራተኞቹ በክረምት መግቢያ ወቅት መንገዶች ዝግ መሆናቸውን የሚገልጹ ምልክቶችን በመንገዶቹ ጠርዝ የእግረኛ መንገድ ላይ የሚያስቀምጡ በመሆኑ መንገዶቹን ለትራፊክ ዝግ ለማድረግ ሲፈለግ ዝግጁ ሆነው ይጠብቃሉ። የሲያትል ፖሊስ መኮንኖች አንድ መንገድ ለማሽከርከር አስተማማኝ አይደለም ብለው ከወሰኑ የተዘጋ መንገድ የሚለውን ምልክት መንገዱ መካከል ያስቀምጣሉ።

ለእርስዎ ደህንነት ሲባል፣ አንድ መንገድ ለማሽከርከር ምቹ ቢመስልዎትም እንኳን መንገድ ዝግ መሆኑን የሚገልጹ ምልክቶችን ማክበር አለብዎ። በበረዶ ጉም ውስጥ ግግር በረዶ ሊኖር ይችላል፣ ወይም ከእርስዎ ዕይታ ውጭ የሆነ አስቸጋሪ ቦታ ሊኖር ይችላል።


የበረዶ/የበረዶ ግግር አገልግሎት ደረጃ
ጎልድ
ሁሉም የጉዞ መስመሮች የበረዶው መጠን መቀነስ በጀመረ በ12 ሰዓት ውስጥ ባዶና እርጥብ ይሆናሉ።
ኤመራልድ
በእያንዳንዱ አቅጣጫ ያለ አንድ የጉዞ መስመር በረዶው መጠን መቀነስ በጀመረ በ12 ሰዓት ውስጥ ባዶና እርጥብ ይሆናል።
Green Lake
Lake Union
Elliott Bay
Lake Washington
DOWNTOWN
SR520 EB

